# ብርሌ ከነቃ አይሆንም ዕቃ
# ግልጽ ደብዳቤ ለ"ኢሕአፓ የአንድነት ሲምፓዚየም" አዘጋጆች፤ በእንግድነት ለተጠራችሁ እንዲሁም በሲምፖዚየሙ ለምትሳተፉ ሁሉ

ከአቶ ሰውየው ሰሜን አሜሪካ
ሰኔ 20 ቀን 2007

ከቅርብ የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አፄ ቴዎድሮስን የምናደንቅበት ዋና ምክንያት በጭካኔአቸው ሳይሆን ከብረት የጠነከረ የኢትዮጵያዊነት ዕምነታቸው፣ የመሪነት ችሎታቸውና ከሁሉም በላይ ያቺ ሰዓት፣ ጀግናውን ከፈሪ የምትለይ፣ የከፍያዋ ዋጋ ከባድ፣ የደም የሕይወት፣ የምንሳሳላት ነፍስን የማጣት ወይም ያለማጣት ጥያቄ ይዛ ብቅ ስትል አፄ ቴዎድሮስ መልሳቸው ለኢትዮጵያ ሀገራቸው ሲሉ ከፊታቸው የተደቀነውን ኃላፊነት ዛሬን ሸሽቼ ነገን በብልሃት የገዛ ወገኖቼ በመሣሪያ ተደልለው እየመሩ ያመጡትን ፈረንጅ ነገ እዋጋዋለሁ ብለው ምክንያት ደርድረው ተገልብጠው አልፈረጠጡም። ከሁሉም በላይ እንደ ኢትዮጵያ መሪነት የሚጠበቅባቸውን የምሳሌነት መራራ ጽዋ ተጎንጭተው ጠላትን ባሳፈረ መልኩ የራሳቸውን ሕይወት ወስደው ኃላፊነታቸውን ተወጥተው ማለፋቸው ኢትዮጵያውያን ሁሉ የምናከብራቸው ትልቅ ባለታሪክ ለመሆናቸው የማያጠራጥረው ለዚህ ነው። በታሪክ እንዳነበብነው ጠላትም ሲሸሽ ከኋላው ነው የመታነው በማለት ራሱን ለማታለል ቢሞክርም የዚያችን ሰዓት የቴዎድሮስን የጀግንነት ታሪክ ከኢትዮጵያውያን ደም ማውጣት ግን አልተቻለውም። ከዚያ በኋላ ታሪክ የሠሩ አባቶቻችንም የቴዎድሮስን ፈለግ ተከትለው  ታሪካቸውን በደም ባጥንታቸው አንሸባርቀው መስወዕትነትን ከፍለው በኢትዮጵያውያን ስነልቡና ታትሞ ለዘለዓለም የሚኖር ትምህርትን አስገብይተው ኢትዮጵያን አስረክበውን አልፈዋል።

ይህን ታሪክ ማውሳት ያነሳሳኝ ዋናው ጉዳይ እንደ አሲምባ ድረ ገጽ አዘጋጅነቴ በቅርቡ ለአሲምባ ዝግጅት ክፍል በአቶ አቡኔና አቶ ስለሺ "ኢሕአፓን አንድ ለማድረግ" ሰኔ 28 ቀን በተጠራ "የኢሕአፓ አንድነት ሲምፖዚየም" ላይ እንድንገኝ ስለተደረገው ጥሪ (የጥሪውን ግልባጭና የስብሰባውን ጥሪ ግልባጭ ከታች ይመልከቱ) በግሌ እንደ አንድ ግለ-ሰብ ያለኝንና የተሰማኝን የግል አስተያየት ለመስጠትና ምናልባትም ይህንን ዝግጅት አድርገናል የሚሉን ወገኖችና ለዚህም ስብስብ መሪ ንግግር አድራጊዎች ብለው የደረደሯቸው ዶክተሮች፣ የኢሕአፓ መሥራች አመራርና አባላት የሚሏቸው፣ የድሮ አባላት በደፈናው ራሳችንን ኢሕአፓ ብለን የምንጠራ ሁላ ለመሆኑ ራሳችንን በመስታወት ተመልክተን ስለራሳችን የምንሰጠው ከፍተኛ ቦታ ተገቢ ነውን? የሚለውን ከራሴ በመጀመር በግልጽ ለማስቀመጥ ነው። ኢሕአፓ ገና ድሮ በልጅነታችን ያስተማረን ሂስና ግለ ሂስ ራሳችንን ከዕውነት ጋር አገናኝተን በዕውቀትና በንቃት ልናድግ የምንችልበት መሠረት ነበር። ለመሆኑ ስንቶቻችን በዚያ ባገኘነው ዕውቀት ራሳችንን ለማዳበር ሞክረናል? ወይስ ባለንበት ረገጥን ወይም ከናካቴዎ የድንቁርናውን ገደል ተያይዘናል? እንግዲህ ለዚህ እያንዳንዳችን የራሳችን መልስ ይኖረናል።

በእኔ እምነት ኢሕአፓን "ለማስተካከል" የተደረገው ድርጅቱን የማፍረስ የተቀነባበረ የውስጥ ትግል ኢሕአፓ እንደ ድርጅት እንዲዳከም፣ ጓዶቻችንን ያስመታ ሁላችንም ነበርን እያልን ራሳችንን ጺላጦሶች አድርገን የምንጎማለል ሁላ የሚያሳፍር የሽሽት ታሪካችን ነው። እስኪ "ሲምፖዚየም" የተባለው ላይ

በእንግድነት እንደ ምሳሌ የተጠሩትን አንዳንዶቹን በኔ መነጽር ልዳሳቸው። ምናልባትም እንደ እኔ ዓይነቱ በአክብሮት ዝም ብሎ ቢቀመጥም ነገሮችን የምንመለከተው ምን እንደሆነ የሚረዱ ከሆነ ለማስቀመጥ እንጂ በግለ-ሰብ ደረጃ አንዳንዶች ትግሉን ባስቀጠሉት ወገኖች ላይ እንደሚያደርጉት ለመዝመት አይደለም። የረቀቀ ዘመቻ የምለው ምሳሌም ለአሲምባ በቅርቡ ከተላከልን የጽሑፍ ዘመቻ ለመጥቀስ ያክል ከዚህ በታች ያለውን ጥቅስ ያንቡ:- ሙሉው ጽሑፍ የተላከልን በአሲምባ ድረ-ገጽ ላይ ወጥቶ ነበር ለተባለ ጽሁፍ መልስ ተብሎ ቢሆንም፣ ጽሑፉን በተጣመመ መልክ በመተርጎም ስለነበርና ዓላማውም በግልጽ ኢሕአፓ ላይ ለመዝመት እንደሆነ ስለተረዳን አላተምነውም ነበር። ለማንኛውም ሁለቱንም ጽሑፎች ከዚህ በታች አያይዤአለሁ።

> ማድረግ ፍጹም አልታሰበንም። ቢያንስ እኔ፤ ያኔም ሆነ አሁንም አምንበታለሁ። አሁን እንደጣዖት ምን ሲባል ኢሕአፓ ስህተት አለው ተብሎ! ለሚሉት፤ ይህ እኔ የማላውቀው ኢሕአፓ ነው። የማውቀው ኢሕአፓ ስህተቱን በግልጽ ከማመን አልፎ፤ ውቀሱኝ ብሎ ባደባባይ የሚቀርብ ነበር። መሪዎቻችን እንደጣዖት መሸከም ሳይሆን፤ ማን እንደነበሩ እንኳን አናውቃቸውም ነበር። አሁን ሚስቶቻቸው እንደ የመጀመሪያ እመቤት የሚከበሩበት ፓርቲ፤ ኢሕአፓ ነው ለማለት ተመልሼ ወደ እናቴ ማህጸን መግባት አለብኝ።

እንግዲህ ከላይ ያሰመርኩበት ጸሐፊው ለማሽሞንሞን የሞከረው እህትና የአመራር አባል የተገናኙት ኢሕአፓ ከሆኑ በኋላ ከሆነ ሁለቱም ወገኖች በኢሕአፓነት ለድርጅቱ ያበረከቱቱ ሊኖር እንደሚችል መገመት አያዳግትም ነበር። በሚያሳዝን ሁናቴ ደግሞ እኔና እሱን የመሰልን ፈርጥጠን ድርጅቱን ጥለን የራሳችንን ኑሮ ስናደላድል በድርጅቱ ላይ በታኞች ያደረሱትን ጉዳት ጠግነው ድርጅቱን ማስቀጠላቸው የሚያስመሰግናቸው እንጂ የሚታፈርበት አድርጎ ማቅረቡ ያሳዘነኝ መሆኑን እዚች ላይ አስቀምጬ ማለፍ እወዳለሁ። እንግዲህ ባጠቃላይ ያለው ዕውነታ ምንድር ነው?

በመጀበሪያ ከራሴ ጀምሮ የታመምነው፣ የሸሸነውና ድርጅቱን በየምክንያቱ ጣጥለን የፈተጠጥን እኛ! ላለፉት 35 ዓመታት ከውጭ ሆነን አሥሩን የምቀባጥር እኛ! ድርጅቱ ውስጥ ቀርተውም ሆነ ተመልሰው ባለ አቅማቸው የሚታገሉትም የተቀበሉትን አደራ ጥለን አንሄድም ያሉ ጀግኖች ብለን ከበሬታ ልንሰጣቸው ሲገባ የምንዘባባትባቸው እኛ። የምናስገርም ማፈሪያዎች የሚነግረን ያጣን እኛ ነን። ያሄንን ስል በራሴ ላይ ግለ ሂስ ለማድረግ ነውና ሰደብከን ተብዬ ደግሞ ስሞታ መስማት አልፈልግም።

35 ዓመት ሙሉ ድርጅቱን እናቃናለን ብሎ የዕድሜ ልክ እንቅስቃሴ በየማግሥቱ የዕርምት እንቅስቃሴ መፈልፈሉ ለኔ ራስን አለማወቅና ዕብደትም ነው። የሰሞኑም "የኢሕአፓ አንድነት ሲምፖዚየም" ዕውን ለአንድነት ወይስ ያንን የፈረደበትን ኢሕአፓን በህብረተሰቡ ውስጥ አሳንሶ ለማሳየት የተቃጣ የጭቃ ጅራፍ? ምናልባት ዶ/ር አበባ በስነ ልቡናዊ ጥናትዋ ብትመረምረው መልካም ነው። አንድ ፕሮጀክትም ይሆናታል።

ለምሳሌ አቶ ክፍሉ ታደሰን ልውሰድ። ይህ ወገን በአመራር ላይ የነበረ ከፍተኛ አክብሮት የነበረኝ ወገን ሲሆን በተለየ ከሠራተኛው እንቅስቃሴ በኩል የመጣሁ ስለ ነበር በሠራተኛ አካባቢ በኢሕአፓ በኩል ተንቀሳቅሶ እንደነበር አውቃለሁ። ከዚያ ውጪ ግን ከ 35 ዓመታት በፊት ትግሉን ለቆ በመሄድ የሽሽት መሪ ለመሆኑ ደግሞ ከራሱ ጋር ቢነጋገር በግልጽ ያገኘዋል። ድርጅቱን ለቆ ከሄደ በኋላ ለናሙና እንኳ የሚሆን የራሱ የሚለው የተሻለ ድርጅት አይደለም የመንደር ዕቁብ እንኳ አቋቋመ አልሰማሁም። የድሮ ኢሕአፓዎች ተሰባስበን ድርጅቱን እንርዳ ወይም ወደ ትግሉ እንግባ የሚል ስብስብ እንደሳንዲያጎ ዓይነቱ ብቅ ሲል ማነው መድረክ ገለ መሌ ብሎ ይፍርሻ ሻጥር ይዞ ብቅ ያለው? አዎን መጽሐፍቶች ጽፎአል። እሱና መሰሎቹ እኮ መስሎኝ የታጠቀን የአንድ ዞን አርማጭሆ የኢሕአፓ ጦር ትጥቁን አስፈትተው ድርጅቱን ለማስተካከል ሱዳን ውስጥ ገብተን ተወያይተን ተጠናክረን እንመጣለን በሚል ሽፋን ትግሉን ጥሎ ለመሄድ ያልተዘጋጀን ጦር ከላይ ያሉት የአመራር አባላት በተለያየ ምክንያት በእኔ ዕምነት ያቺ ሰዓት የምትጠይቀውን መራራ የመሪነት ጥዋ ከመጎንጨት ይልቅ ድርጅቱ የሚፈርስበትን ያመቻቹት? ያ ብቻም እኮ አይደለም፣ የተቀበረውን ትጥቅ ወጥቶ ላካባቢው ሕዝብ እንዲሰጠው እንኳን አይደለም የተደረገው። ከብተናው የተረፉት ተደራጅተው መንቀሳቀስ ዜና ሲሰማ በነሱ እጅ እንዳይገባ የሱዳን መንግሥት አውጥቶ

እንዲወሰድ መርተው ያስወሰዱትም እነሱው ናቸው። ገንዘብም ተሠርቶበታል የሚልም ሃሜታ እኮ አለ። ለመሆኑ ስለዚህ ሁሉ ግለ-ሂስ አድርገው ያውቃሉ? ወይስ እነሱ መልእክት አብረዋቸው የነበሩ ዛሬም በትግሉ ላይ ያሉት ግን ጋኔኖች? በምንስ ሞራል ብቃት ዛሬ ደግሞ ኢሕአፓን አንድ ለማድረግ በሚል ፈሊጥ እንደበግ ሊነትቱን ይሞክራሉ? ወገንን መናቅ አይሆንም? ወይንስ አክብሮትና ዝምታ ሞኝነት ተባለ?

ለነገሩማ አቶ ክፍሉ እኮ ወያኔ ያሠራው መስሎት ኢትዮጵያ ገብቶ 97 ላይ አይደለም እንዴ አገር ለቆ የወጣው? ስለዚያም የጻፈውን አንብቤአለሁ። ሌሎቹም ከወያኔ ጋር ገብተው ሆሆ ብለው ተተፍተው የወጡ መሆናቸውን ያደባባይ ሚስጥር መሁኑን እባካችሁ ንገሯቸው። ታዲያ ተደራጅተን ተሰባስበን ጠንካራ ኢትዮጵያዊ ድርጅት መመሥረቱ አጠያያቂ አለመሆኑ ይጠፋቸዋል ለማለት ይቻላል? እንደ ምሳሌ አቶ ክፍሉን እዚህ ላይ ላንሳ እንጂ ሮባም እኮ ቢሆን በአንድ ወቅት የሠራዊቱ ኮማንደር የነበረ ከሁሉ በፊት ጥሎ የሸሸ ለብዙዎቻችን ተስፋ መቁረጥና መበተን ምክንያት መሆኑን ከራሱ ጋር ተነጋግሮ ለመሆኑ ያውቃል? የአንድ መርከብ ዋና አዛዥ ማዕበል ሲመጣና መርከቧ መስጠሟ እንደማይቀር ሲረዳ ከተሳፋሪዎች ቀድሞ ነፍሴ አውጪኝ እንደማለት እኮ ነው። ያም ሆኖ ብዙዎቻችን እንዲህ አስከዳችሁን ብለን መሪዎቻችንን አልፈረድንባቸውም። ታዲያ አላርፍ ሲሉ ደግሞ ኸረ እየተስተዋለ ብንል አይፈረድብንም። አቶ መርሻም እንዲሁ ብናከብረው የቀድሞ ጓዶችን በማሰባሰብ ሰበብ አብረው ከጎኑ የታገሉትን ሊከዳ ሲከጅል ሊፈጥር ላሰበው የአንጃ ድርጅት ተጎታች ለማድረግ እንደእኔ አይነቱን ሊጠቀም ሞክሮ ታዝበን የተውነው ወገን አይደል? አጠፋሁ ግለ-ሂስ ሲል አልሰማንም። የሰማነው በመሪነት ያገለገለውን ድርጅት ጉባኤ ሄድኩ እንኳን ሳይል በሌሊት ተሰውሮ የጠፋ በምን አኳኋንና ሞራል ብቃት "የኢሕአፓ አንድነት ሲምፖዚየም" ብሎ እንደእኔ አይነቱን ሊሰብክ ይሞክራል? ኢሕአፓ ዴሞክራሲያ ብሎ የወጣው መርሻ ራሱ የሚመራው ድርጅት ተብዬ ብትንትኑ አይደል እንዴ የወጣው? ያውም ወርደው በዘር ሳይቀር ሲናከሱ በኢሜል ሲናከሱበት የበረውን ታሪካቸውን ሁሉ መዝግበን አሰባስበን ይዘናል። እናውቀዋለን። እኔ የሚገርመኝ ይሄ ሁሉ ንቀት ወይንስ አለማወቅ? አያ ጅቦ የማያውቁት ሀገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል። መርሻም እንዲሁ የማያውቁት ጋ ሄዶ ሸንጎ ይበል። ያም ቢሆን ደግሞ ሸንጎ ውስጥም ያለው ስብስብ ጣቱን የሚጠባ ስላልሆነ ማንነቱን አጥቶት አይደለምና እንደኔ ዓይነቱ ደግሞ ግም ለግም አብረህ አዝግም ማለቱ አይቀርም።

ለማጠቃለል፡-

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ግለሰቦችን ለማብጠልጠል አይደለም። ያለውን ዕውነታ በማስቀመጥ የዚያ ትውልድ ብለን እራሳችንን የምንክብ ሁላ ሕይወታቸውን በሙሉ ለትግሉ ሰውተው ዛሬም በኢሕአፓነት የኢትዮጵያዊነት አጀንዳን ከፍ አድርገው የሚታገሉትን በሰበብ አስባቡ ከመቀጥቀጥ እስኪ የራሳችን የምንለው ድርጅት እንፍጠርና ምሳሌ እንሁን። በኢሕአፓነት የምንቀጠቅጣቸው ወገኖች ኢትዮጵያዊነትን ከድተው አያውቁም። በትግል ስም የወጡበትን ዓላማ ስተው ከማንም አንጎናብስም ነው ያሉት። ሰሚ አጡ እንጂ። ብግለ-ሰብ ላንወዳቸው እንችላለን፣ ነገር ግን ትግሉን ከዱ የሚል ግን የለም። እኛ ካልሆነልን ኢሕአፓን ለታጋይ ኢሕአፓዎች እንተወው። አብረን ለሠራነው ሁላችንም ተጠያቂዎች ነኝ። ዛሬ ዛሬ የማያባራ የዕርማት እንቅስቃሴ በሉት ኢሕአፓ-ዴሞክራሲያዊ ኢህአፓን የማፍረስ እንቅስቃሴ እንጂ ምንም ገንቢነት ሊሆን አልቻለም! አይችልምም።እነሆ ዞር ብለን ያለፈውን እንቅስቃሴአቸውን ብንመለት እኮ የክህደት የፍርሻ ታሪክ እንጂ አኩሪ የማደራጀትና የማሰባሰብ ሥራ አየሁ የሚለኝ ያሳየኝ። እንደ ምሳሌ በዋሺንግተን ዲሲ የነበረውን የኢሕአፓ የሕብረት ራዲዮ ጣቢያ እንደ ምሳሌ ብንወስድ፣ በአንጃኝነት የተንቀሳቀሱ ወገኖች ቁልፉ በጃቸው ስለነበር ብቻ የራዲዮ ጣቢያውን ይዘው ሄደው ነበር። ለመሆኑ ምን ያህል ጊዜ ሠሩበት? በአንጻሩ ተደራጅቶ የቀጠለው ክፍል ግን ዛሬ የፍኖተ ራዲዮ ጣቢያን የሳተላይ ራዲዮ ድረስ በተደራጀ መልክ ፕሮግራሙን ቀጥሎአል። ተደራጅቶ ትግሉን ያስቀጠለ ወገንና የብተናው ወገን ሲነፃጸር ይህን ይመስላል። የሳተላይቱን ራዲዮ ወያኔ እያዳፈነባቸው ስለሆነ ይልቅስ ተሰባስበን ማጠናከር አይሻለንም? ታሪካችንን ለሚቀጥለው ትውልድም ማስተላለፍ እኮ አብረን የኮመሰስነውን ሁላ ወዳጅ ጠላት እስኪሳለቅብን ድረስ ባገኘነው መንገድ ሁሉ አሥሩን በመቀባጠር አይደለም። ከራሴ ጀምሮ

ትግሉን ለቀን የሄድንበትን ምክንያት እያንዳንዳችን ከራሳችን ጋራ እንነጋገርና እንመርምር። የትግል ታሪክ ለሚቀጥለው ትውልድ የሚተላለፈው ያ ታሪክ ሊድበሰበስበት የሚችልበትን ሁኔታዎች በማመቻቸት አይደለም። ስለሆነም በነገው እሁድ የተጠራው የፍርሻ ሲምፓዚየም ላይ እንደማልገኝ በግልጽ እያስታወቅሁ ይህ ሲፖዚየም ምንም ፋይዳ የማያመጣ መሆኑን ከሰብሳቢዎቹና ከስብስቡ በመተማመን መናገር እችላለሁ። ዘለዓለማቸውን የትግሉ ማዕከል ሕዝቡ ሳይሆን ራሳቸውን ከፍ አድርገው የሚመለከቱ በሽተኞች እንጂ መሪዎች ሆነው ሊወጡ አልቻሉም፣ አይችሉምም። ሁኔታው ጠጠር ሲል መገልበጥ፣ ሽብረክረክ ብሎ እጅ መስጠት ወይ መፈርጠጥ እንጂ ባመኑበት በጽናት መቀጠል አይቻላቸውም። የዚያች ሰዓት ጥያቄ መልስ መስጠት የማይችሉ ናቸው። በዚህ ጽሁፍ ለማለት የፈለግሁትም ይሄንኑ ነው። ያገሬ ሰው ብርሌ ከነቃ አይሆንም ዕቃ ይላል። ያቺ የመሪነት ቀውጢ ሰዓት ያቀረበችላቸውን ጥሪ ረጋግጠው የፈረጠጡ ሁላ በምንም ዓይነት መሪነትን ይሰጣሉ የሚል ዕምነት ከቶውንም የለኝም። በተቃዋሚው በኩል ሊስተካከል የሚገባውም ችግራችን አስመሳዩን ቴዎድሮስና ዕውነተኛውን አበራይቶ መለየቱ ላይ ነው።

ኢሕአፓን አንድ በማድረግ ስም የሚገፋው የፍርሻ ዘመቻ ይቁም!
ኢሕአፓ አንድና አንድ ብቻ ነው!

አቶ ሰውየው ከሰሜን አሜሪካ
ሰኔ 20 ቀን 2007 ዓ.ም.

ለአሲምባ አስተዳደር

ከሁሉ አስቀድመን የከበረ ሰላምታችን እያቀረብን ኢህአፓን አንድ ለማድረግ በፈረንጆች አቆጣጠር በሰኔ ወር መጨረሻ ታላቅ ጉባኤ በዋሺንግተን ዲሲ ለማድረግ በዝግጅት ላይ ነን። አገራችንን ከገጠማት አስቸጋሪ ሁኔታ ለማውጣት አገር አቀፍ ድርጅቶች መሰባሰብና መጠናከር አለባቸው ብለን እናምናለን። ስለዚህ ነው ኢህአፓ ዴሞክራሲያዊና የኢህአፓ የእርምት እንቅስቃሴ እንዲሁም ለረዥም ጊዜ ከትግሉ እርቀው የነበሩ ነባር አባላት በመዋሃድ ኢህአፓን አንድ ለማድረግ ቆርጠው የተነሱት። ስለሆነም በሰኔን 28 ቀን 2015 ዓ.ም በሚደረገው የአንድነት ጎባኤ የመክፈቻ ቀን እርሰውም በቦታው ተገኝተው የዚህ ታሪካዊ የመከፈቻው ጉባኤ ተካፋይ እንዲሆኑ በአክብሮት ተጋብዘዋል። በዚህ የጉባኤ መክፈቻ ቀን የኢህአፓ መሥራች አባላትና ታዋቂ ምሁራን የጥናት ጽሁፍ ያቀርባሉ። ለምሳሌ አቶ ክፍሉ ታደሰ፤ ዶ/ር መላኩ ተገኝ፤ አቶ አብዲሳ አያና፤ ዶ/ር ሙሉጌታ ሰዩም፤ ዶ/ር ደምሴ ኦሉማ፤ እንዲሁም ሌሎች። ከጥናት ጽሁፉ በኋላ በወቅታዊ ሁኔታ ላይ ሰፊ ውይይት ይደረጋል።

ጉባኤው የሚደረግበትን ቦታ Howard University Blackburn Forum

ጥያቄና አስተያየት ካለዎት በዚህ ስልክ ቁጥር ሊያገኙን ይችላሉ

አቡኔ ብር 323-332-8838

ስለሺ ንጉሤ 619-727-3030

እናመሰግናለን



**ቀኑ ይለወጣል**

የትላንቱ ችግር ነገ ላይ ተረት ነው፤
ያሳለፍነው ስቃይ ወደፊት ክብር ነው።
በዛሬ ውስጥ ሆኖ ፈተናው ቢከብድም፤
ይለወጣል ቀኑ ዛሬ ነገ አይደለም።

(ከአልታወቀ ገጣሚ)



# Let us come together!
# የኢሕአፓ አንድነት ሲምፖዚየም



## ኢሕአፓን አንድ ለማድረግ በተጠራው የመክፈቻ ጉባኤ ላይ ተካፋይ እንዲሆኑ በአክብሮት ተጋብዘዋል፡፡

ለሕዝብ ይፋ በሚደረገው የኢሕአፓ አንድነት ሲምፖዚየም የመክፈቻ ሥነ ስርዓት ላይ የኢህአፓ መሥራቾች ፤ በኢሕአፓ ድርጅት ውስጥ በልዩ ልዩ እርከን አመራር ይሰጡ የነበሩ እና ሌሎችም ምሁራን በአገራችን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የጥናት ጽሑፍ ያቀርባሉ። በሚቀርቡት ጽሑፎች ላይ ሰፊ ውይይት ይደረጋል።

## የጥናት ጽሑፍ አቅራቢ እንግዶቻችን

አቶ ክፍሉ ታደሰ (የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ)
ጋዜጠኛ አበበ በለው (አዲስ ድምጽ ሬድዮ አዘጋጅ)
ዶ/ር ደምሴ ኡሉማ (ፌደራሊዝምና የጎሳ ፖለቲካ)
ዶ/ር መላኩ ተገኘ (የኢትዮጵያ ኢኮኖሚና ማህበራዊ)
ዶ/ር አበባ ፈቃደ (አዕምሮአዊ ለውጥ ለሀገራዊ ራዕይ)
ዶ/ር ሙሉጌታ ስዩም (የኢትዮጵያ አንድነትና የጎሳ ፖለቲካ)
ዶ/ር ፍጹም (ወጣቱና የኢትዮጵያ ፖለቲካ)
ወጣት ታዘበው አሰፋ (የኢትዮጵያ ወጣቶች በኢሕአፓ ትግል ትናንትና ዛሬ)
አቶ መርሻ ዮሴፍ (ማጠቃለያ)

**እሁድ፥ ሰኔ ፳፩ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም (Sunday, June 28, 2015)**

**Howard University Blackburn Forum**

**ከ 1:00 pm ጀምሮ**

የኢሕአፓ አንድነት ጊዜአዊ ኮሚቴ

ያደራ ቃል

ለሕዝቦች ሰላም ተገዝተዋል፤
ለፍትህ ሞትን ገብረዋል፡፡
ባሳዩት መንገድ በአመንበት፤
ቆመን ለአንድነት ለእኩልነት፡፡

ትግሉ ቢረዝም ጊዜ ቢወስድ፤
ፈታኝ ነውና የእውነት መንገድ፡፡
ፍትሃዊ ትግል ይቀጥላል፤
ሕዝባችን ሁሌም ያቸንፋል፡፡

# አንዱዓለም ስለ ኢሕአፓ ከሰጠው 9 አስተያየቶች በ7ቱ ተሳስቷል

ከመልካሙ በረከት

አንዱዓለም ተፈራ ትግላችንን እንመርምር በሚለው ጽሁፉ ትግሉን ሳይሆን ድርጅቶችን ሲመረምር በማየቴ ገርሞኛል፡፡ ርዕሱ ድርጅቶችን አንመርምር ቢለው ሳይሻል ይቀር? ያምሆነ ሌላ ስለ ኢሕአፓ የጻፈው መረቅ የሌለው ነው፡፡ በግምት ወይም እንደ አንዱዓለም በስማ በለው አይደለም የምጽፈው፡፡ የድርጅቱ አባል በመሆነ የማውቀውን ነው የምጽፈው፡፡ በርግጥ ጸሃፊው ሁለት ሃቆችን ተናግሯል፡፡

አንደኛው ኢሕአፓ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው ከዳር እስከ ዳር በሕዝብ የተደገፈ የፖለቲካ ድርጅት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ከአርባ ዓመት በላይ ዕድሜ ያስቆጠረ ጠንካራ ድርጅት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ጸሃይ የሞቀ ዕውነት ነው።

<u>ከጸሃፊው ጋር የማልስማማባቸው ሰባቱ ነጥቦቹ፡-</u>

1. መቼም ሶስት አባላት የያዘም ድርጅት ከተባለ "<u>እስከመቼም</u>" ድርጅት ሊባል ይችላል። ነገ ደግሞ <u>እስከመቼ ዴሞክራሲያዊ</u> የሚል ቢፈጠር መገረም የለብንም፡፡ **በመካከላቸው ያለው ልዩነት እንኳን ለውጭው ኢትይዮጵያውያን ለርራሳቸው አባላት እንኳን የውጭው ሰው አባላልቱ አባላት ግልጽ ሳይሆን**. . . እንዴት ተደርጎ አንዱዓለም? ልዩነታችንማ የሰማይና የምድር ያህል ይራራቃል፡፡ የአርባ አመት የትግል ልምድ ያለን እንዴት አድርገህ ልዩነት የማናውቅ አድርገህ እንደገመትከን ገርሞኛል፡፡ ልዩነታችንን ለማወቅ በርካታ ጽሁፎች ተጽፈዋልና አንብብ፡፡ ወይም አጠገብህ ካለ አንድ ኢሕአፓ ለመረዳት ሞክር፡፡ የተለያየነው በመርህ ደረጃ ነው ሁሉን ትቼ ባጭሩ፡፡

2. **ግማሽ እግራቸውን (አንድ እግራቸውን ለማለት መሰለኝ) በትላንት ትግላቸው ሌላውን ደግሞ በምኞታቸው ተክለው** . . . ምን ለማለት እንደተፈለገ አልገባኝም፡፡ ቀና አባባል ይሆን ወይም ሰንካላ ለመረዳት አልቻልኩም፡፡ ምናልባት በሌላ ጽሁፍ ካልሰለቸው ያብራራ ይሆናል፡፡ ነገና ተነገወዲያ መሰረታቸው ትናንት አይደለም እንዴ?

3. **የትግሬዎች ነጻ አውጭ ግንባር መንግስት በሰላምም ሆነ በትጥቅ ትፍልም መወገድ አለበት ብለው በፓለቲካ ምህዳዳሩ አሉ** የሚለው የሃቀኛው ኢሕአፓ ኣቅዋም እንጅ የአንጃው አይደለም፡፡ አንዱ ልዩነታችን ይሄ ነው፡፡ አታደባልቀን፡፡ የሰላሙንና የመሳሪ ትግሉን <u>ሁለገብ ትግል</u> ነው የምንለው፡፡

4. **እንደ ሰማያዊ ፓርቲው ግልጽ አውጥተው ሕዝብ እንዲያውቀው ባያደርጉም እንደ ግንቦት ሰባት የተሸፋፈነ አይደለም።** ምኑን ነው ለሕዝብ ኢሕአፓ ግልጽ ያላደረገው? ምን ከሕዝቡ የደበቀው ጉዳይ አለ ይህ ላለፉት አርባ ሶስት አመታት በሕዝብ ታቅፎ የሚታገለው ኢሕአፓ? ጸሃፊው ስለኢሕአፓ ብዙም ባለማወቁ ሕዝቡም የኢሕአፓ ዓላማ አያውቅም ሊል ወስኗል፡፡

5. **እንደሌሎቹ ሁሉ አብዛኞዎቹ መግለጫቸው የወጡትና ሕዝብ የሚያውቃቸው የገዥውን ቡድን በማውገዝና ወንጀሉን በመዘርዘር ላይ ያተኮሩ ናቸው።** እና ገዥውን ቡድን ማውገዝ የለብንም

ነው አባባሉ፡፡ ሕዝቡ የሚያውቀውን ማለትስ ምን ማለት ነው፡፡ ሃቅ ቢደገም ምን ይከፋል፡፡ ውሸትን አይደለም የደገሙት፡፡ ቃሉ ጠፋው መሰለኝ ሊለን የፈለገው ተግባራዊ አይደላችሁም ለማለት ነው፡፡ ሰማይ ላይ ተቀምጦ በአጉይ መነጽር ኢሕአፓ ምን እንደሰራ ወይም እንደሚሰራ ማየት እንዳልቻለ ተረድቼዋለሁ፡፡ ዕውነትን መናገር ስድብ አይደለም፡፡ ወያኔ መጥፎ ነው ማለት ስድብ አይደለም፡፡ ቢሰደብም ለወያኔ አይበዛበትም፡፡ ከመሳደብ በላይ ልናጠፋው አይደል ትግላችን?

6. **ለምን አመርቂ የሆነ ትብብር ከሌሎች የትግል ድርጅቶች ጋር ፈጥረው መሄድ እንዳልቻሉና በተለይም በመካከላቸው ስምምነት ፈጥረው ለምን ወደፊት እንደማይሄዱ ለኔ ግልጽ አይደለም፡፡** ኢድሃቅንና ሕብረትን ብቻ ማንሳቱ ኢሕአፓ ከበርካታ ድርጅቶች ጋር አብሮ መስራቱን ማስታወስ በቂ ይመስለኛል፡፡ ምናልባት አነዚህን ሕብረቶች አልሰማህም ለማለት ይከብደኛል። ድርጅቱ አሁንም የሕብረት ጥሪ አቅርቧል፡፡ መስፈርቶችም አስቀምጧል፡፡ ምናልባት አልሰማህ ይሆናል፡፡

7. **ከቅርብ ጊዜ ሁለቱን ለማቀራረብ የተደረገው ጥረት በአንደኛው ወገን ተቀባይነት እንዳላገኘ ተረድቻለሁ፡፡** አንጃው ለመታረቅ ፈቃደኛ ሆኖ ኢሕአፓ እምቢተኛ ሆነ ተብለህ ነው የተነገረህ፡፡ ለምን ወደ ኢሕአፓ ጽ/ቤት ደውለህ እስቲ አስረዱኝ ለማለት ለምን ከበደህ? የሌሎቹ ድርጅቶች መከፈል ሳያስገርምህ የኢሕአፓ ለምን? በነገርህ ላይ አንጃ ለኢሕአፓ አዲስ ክስተት አይደለም፡፡ አንጃነት የሚፈጠረው በመርህ ካለመግባባት ነው፡፡

ጸሃፊው ሲያጠቃልል ሕዝብ የሚያውቀውን አዲስ ያልሆነ ጉዳይ ነው፡፡ ደግመው ደጋግመው ቢችሉም ሁሌ ይህንኑ አባባል ቢደግመው ይደገፋል እንጅ **ሁሉ ሰው የተናገረውን** ብለን ልናሾፍበት አይገባም፡፡ ጸሃፊው ስለ ኢሕአፓ ያለው ግንዛቤ የተሟላ አይደለም፡፡ ሃቁን በሚገባ ስትረዳ ይህ ድርጅት ያኮራሃል፡፡ ወይም ሬዲዮ ስርጭቱን አዳምጥ፣ ፕሮግራሙን አንብብ፣ በርካታ ጹፎቹን አገላብጥ፡፡ በርግጥ የ43 አመትን ታሪክ መመርመ ቀላል አይደለም፡፡ የሚቀለው ግን በትዕግስት ለጥያቄዎችህ ሁሉ መልስ የሚሰጡ ስላሉ ደውልላቸው፡፡ኢሕአፓ በተሳሳተበት ሁሉ ስህተቱን ገምግሞ ሂስ አቅርቦ እርማት ወስዷል፡፡ አካፋን አካፋ ማለቱ ትክክል ሲሆን አካፋውን ዶማ ማለት ግን ስህተት ነው፡፡

# በአሲምባ ድረገጽ የተሠጠኝ መልስ የድርጅቱ ነው።

ረቡዕ፤ ግንቦት ፲፭ ቀን፤ ፳ ፻ ፯ ዓመተ ምህረት ( 5/23/2015 )

በርግጥ አሁን ያለንበት የእደጥበብ ዕድገት ሂደት፤ ብዙ የትናንት ጉዳዮችን ለውጧል። ጫር ጫር አድርጌ በድረገፆች በመለጠፍ፤ በቅጽበት ጋዜጤኛ ተብዬ ልቆጠር እችላለሁ። በፓልቶክ ክፍል ተቀምጬ በመዋልና ገዥውን ቡድን በማውገዝ፤ ታጋይ ነኝ ልል እችላለሁ። የተለያዬ የብዕር ስም በመጠቀም፤ የደርጅት አይደለም፣ የግለሰብ ነው፣ ሌላም ማምለጫ ቀዳዳዎችን ለመፍጠር በሚያስችለኝ መንገድ፤ ሌሎችን ሳብጠለጥል ውዬ፤ ታገልኩ ማለት እችላለሁ። ሰዎችን እንዳፈተተኝ በማብጠልጠል፤ ሌሎችን ማሳነሱን ሙያዬ ብዬ በመያዝ አይታወቅም ማለት እችላለሁ። አዎ! አንድና ሁለት ሰዎችን ይዤ ድርጅት አለኝ ማለትም እችላለሁ። ያን ሁሉ እንዲቻል ያደረገው፤ የዘመናችን የእደጥበብ የዕድገት ደረጃ ነው። ይህ ሁሉ፤ ጣትን ባሳረፉበት የኮምፒውተር ማቀንቀኛ ጠቋሚ፤ ባጭር የዘክዝክ ምርምር፤ ምንጬንና እውነተኛ ግቡን መረዳትም ይቻላል። እኔ ስጽፍ፤ እውነተኛ ስሜን በመጠቀም፤ አንዱዓለም ተፈራ ብዬ፤ በብዕር ስም ጀርባ ሳልደበቅ ነው። አወጡትም አላወጡትም፤ ጽሑፎቼን ስልክ፤ ለዚህ ወይንም ለዚያ ድረገጽ ብቻ አላልኩም። ለሁሉም ልኬያለሁ። ለአሲምባ፣ ለኢካዴፍ፣ ለሚያወጡልኝ፣ ላላወጡልኝ።

ለኔ በአሲምባ ድረገጽ የተጻፈው መልስ፤ **<u>አንዱዓለም ስለኢሕአፓ ከሰጠው 9 አስተያየቶች በ7ቱ ተሳስቷል</u> - ከመልካሙ በረከት፤** ያለምንም ማቅማማት፤ ይህ ቅን በመሰለ ርዕስ ተሸፍኖ በስድብ ያጌጠው ጽሑፍ፤ የድርጅቱ መልስ ነው። ቀደም ብሎ፤ በተናጠል ከድርጅቱ ደጋፊዎች በተላኩ የኢሜል መልዕክቶች፤ ተመሳሳይ ነጥቦች ተወርውረውልኛል። ስለኢሕአፓም ሆነ ሰለሌሎቹ ታጋይ ድርጅቶች ስጽፍ፤ መነሻዬና መድረሻዬ፤ አሁን የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ያለበት ሀቅ ነው። አሁን ካለብን ኃላፊነት ተነስቼ ነው። በምንም መንገድ የትናንቱን ትግል ወቃሽ አይደለሁም። በኔ እምነት፤ ትናንት ኢሕአፓ ባደረገው ማንኛውም በጎም ሆነ የተሳሳተ ድርጊት፤ አብሬ ተጠያቂ ነኝ። ድርጅቱ ከመታወጁ በፊት ጀምሮ፤ የፓርቲው አባል ነበርኩ! የሠራዊቱም አባል ነበርኩ! ለኔ ሰለኢሕአፓ ምንነትና ማንነት ለማስተማር መሞከር ችግር ላይ ይጥላል። በነገራችን ላይ፤ ትናንት ወጣቶች በኢሕአፓ ተሰባሰበው ያደረጉት ትግል፤ ቀድሞ በፋሽስቱ ወረራ ጊዜ ኢትዮጵያዊ ወጣቶች እንዳደረጉት ትግል ሁሉ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክና ሀብት ነው። ማንም የግል ወራሽ የለውም። ዛሬ በማንኛውም ድርጅት ተሰባስበው፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት የሚታገሉ ሁሉ፤ የዚያ ትግል ቀጥተኛ ባለቤቶችና ወራሾች ናቸው። ትግሉ ሕዝባዊነቱ እዚህ ላይ ነው። አሁን ባንድ ስም ወይንም በሌላ ተደራጅቶ፤ እኛ ብቻ ባለቤቱቹ ነን ማለት፤ የሕዝብ ትግልን ባለቤትነት ጥያቄ ውስጥ አስገቢ ነው። እናም ተው!

ትናንት ኢሕአፓ ያደረገውን ተጋድሎ፤ በምንም ዓይነት አላንቋሽሽም። በአንጻሩ ደግሞ፤ ዛሬ ማንም ድርጅት የዚያ ትግል የግል ባለቤት ነኝ ሲል፤ በቀላሉ እስቃለሁ። እኔም የባለቤትነቱ ተካፋይ ነኝ ብዬ ከልቤ ስለማምን፤ ለጉድለቱም ለስኬቱም! ከእህትና ወንድሜ ጀምሮ፤ እስከ ውድ አብሮ አድግና የጊዜው ጓደኞቼ ድረስ ተሳትፌበታለሁ። በሂደቱም ከወንድም በላይ ያቀርብኳቸውን፣ የትምህርት ቤት ጓደኞቼን ሠይፉ ጠና፣ እዮብ ጠና፣ ዓይነተኛ ተምሳሌዬን ብርሃን እያሱን፣ የሰንዳፋ ፖሊስ ወታደሮች (በተለይ እንዳለና ሽመልስ)፣ የከተማው ትጥቅ ትግል ጓዴ የአየር ወለዱ የ፻ አለቃ መርዕድ (ያሬድ)ን፣ ሌሎችንም አጥቼበታለሁ። ወጣት የአዘዞ ልጆችን፣ አበባው መኮነን፣ አላምረው በላይ፣ ብርሃኑ ኃይሉ፣ ዓለምነሽ ኃይለማርያም፣ ትውረስ ገብረየስ፣ የዝና ታደስን አጥቼበታለሁ። እኒህ የግል የኔ ብቻ አይደሉም። ከኔ የበለጠ የሚወዷቸውና የሚቀርቧቸው አሉ። ለኔ ደግሞ በራሴ መንገድ ውዶቼ ነበሩ። በትግል ሜዳው ላይ፣ በስኳድ አብረውኝ ከነበሩት ከእያሱ፣ ይልማና ስዩም ሌላ፣ ተሰማ ሐኪሙን ወልቃይት ላይ፣ ራሴ ባካባቢው መልምዬ ለትግሉ ከጋበዝኳቸው አርሶ አደር ወጣቶች አንስቶ፤ አብረን ከከተማ ወጥተን፣ በዚያው ተሰውተው የቀሩ ብዙ የግል ጉዳቶች አሉኝ። ለዚህ ነው አሁንም የዚያ ታሪክ ባለቤትነቴ። እናም በአሲምባ ጽረገጽ፤ እኔን ስለኢሕአፓ ሊያስተምሩኝ ሞክረዋል! በምንም ዓይነት ወጣቶች በኢሕአፓ ተሰባስበን ያደረግነውን ተጋድሎ አልኮንንም። የኔ ነው። እንዲያውም፤ ያኔ የነደፈኝ የትግል ንብ፤ በየቦታው ስለኢሕአፓ መጥፎ አታንሱብኝ ያልኩባቸውና የምልባቸው ወቅቶች ብዙ ነበሩ፤ ናቸውም። ለኔ ስለኢሕአፓ ሊነግሩኝ ሞከሩ!

ትግል፤ ወርጠውና ወደው የሚሸከሙት ጫና ሳይሆን፤ ታሪካዊ ወቅቱ ለሚጠይቀው ኃላፊነት፤ በዚያ ትውልድ የተገኙ አባላት፤ ቆመው በሚቆጠር፤ ራሳቸውን የሚያስመዘግቡበት አኩሪ ድርሻ ነው። በ<u>፲፱፻፷፯</u> ዓመተ ምህረት ዙሪያ ለነበርነው ወጣቶች፤ በተማሪ ትግሉም ሆነ በኢሕአፓ ስንሰለፍ፤ የወቅቱ ታሪካዊ፣ ትውልዳዊና ሀገራዊ ጥሪ፤ ኃላፊነቱ ተሰምቶን ነበር። ኢሕአፓ መታገያ መሣሪያችን እንጂ፤ የተሸከምነው ጣዖት አልነበረም። የሕዝቡ ድል ማድረግ እንጂ፤ የኢሕአፓ ድል

ማድረግ ፍጹም አልታሰበንም። ቢያንስ እኔ፤ ያኔም ሆነ አሁንም አምንበታለሁ። አሁን እንደጣዖት ምን ሲባል ኢሕአፓ ስህተት አለው ተብሎ! ለሚሉት፤ ይህ እኔ የማላውቀው ኢሕአፓ ነው። የማውቀው ኢሕአፓ ስህተቱን በግልጽ ከማመን አልፎ፤ ውቀሱኝ ብሎ ባደባባይ የሚቀርብ ነበር። መሪዎቻችን እንደጣዖት መሸከም ሳይሆን፤ ማን እንደነበሩ እንኳን አናውቃቸውም ነበር። አሁን ሚስቶቻቸው እንደ የመጀመሪያ እመቤት የሚከበሩበት ፓርቲ፤ ኢሕአፓ ነው ለማለት ተመልሼ ወደ እናቴ ማህጸን መግባት አለብኝ።

በትናንት እግርን ተክሎ አልነቃነቅ ያለን ሰው፤ ስለዛሬ ችግርና መፍትሔ እናውራ ቢሉት፤ የዛሬው ችግር አይታየውምና፤ የእውቀቱ ወሰን ስለሚያግደው፤ ዓይኑ መገለጥ አይቻለውም፤ መልሶ መላልሶ ያንኑ ከመደረት በስተቀር! ለኔ ትናንት የደርግ ሰዎች ያደረጉት በደል፤ አፍንጫዬንም ይዤ ቢሆን፤ ጠባሳው አሁንም አይልቀቀኝ እንጂ፣ አእምሮዬ አሁንም አይርሳው እንጂ፤ ዛሬ ማድረግ ላለብኝ ተግባር፤ ወሳኝ አይደለም። ዛሬ አእምሮዬን አጣቦ የያዘው፣ የዚህ ድርጅት ስም ወይንም የዚያ ድርጅት የትናንት ተግባር ሳይሆን፤ የዛሬውን ዋነኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት፤ የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር ቡድንን ለማስወገድና አስተማማኝ ነገ እንዲኖረን፤ መላ ታጋይ ዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያዊ ኃይሎችን ማሰባሰብ ነው። ይሄን ቡድን በማስወገድ፤ ትናንት በወጣትነቴ የታገልኩለትንና በተደጋጋሚ የቆሰልኩለትን የኢትዮጵያን ሕዝብ ሉዓላዊነትና የኢትዮጵያ ነፃ መውጣት፤ ገሃድ ሆኖ ማየት እፈልጋለሁ።

እኔን በግለሰብ ማብጠልጠል ማንን ይጠቅማል? ማነውስ ሊያደርገው የሚፈልገው? በትግሉስ ላይ ምን ጠቀሜታ አለው? ለትንሹም ሆነ ለትልቁ ጽሑፍ መልሰ መሥጠትና በስድብ ማኾነርኃር ትግል ነው? ይሄ ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከታጋዩ ወገን የሚጠብቀው? በትግሬዎቹ ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት ላይ ማላዘንና መፎከር ነው ትግል? ተግባሩ የት ላይ ነው? የተነሳሁት እኮ ትግሉን ወደፊት ለማንቀሳቀስ ማድረግ ያለብኝና የምችለውን ለማበርከት ነው። ሙያዬ ብዬ የያዝኩትና የምተዳደርበት ሥራ እኮ አይደልም! እንዴት ያለ ጉድ ነው? ለሀገሩ ሰው የምችለውን ላድርግ ብሎ መነሳት፤ ለመብጣልጠል ይዳርጋል? ለያውም ታጋይ ነን በሚሉ!

ከትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር አባልትና ደጋፊዎች ብዙ ስድብና ማስፈራሪያዎች ደርሰውኛል። የጠበቅሁት ነው። እንዲህ ዓይነት ከታጋዩ ወገን ይደርስብኛል ብዬ ግን አልጠበቅሁም። ለዚህም ነው የትግል ታሪካችን ዓመት ከመቁጠር ያለፈ ያስመዘገበው ብዙ የሌለው። ትግሉ ግን፤ በግለሰብ እንዲህ ወይንም እንዲያ ማደረግ አይጀመርም፤ አይጨረስም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለበት የኑሮ ሀቅ ተመሥርቶ በትግል ላይ  ነው። በሀገር ቤት እውነተኛ ታጋዮች ከፍተኛውን መስዋዕትነት እየከፈሉ፤ እየታገሉ ናቸው። በነሱ ላይ ትልቅ ተስፋ አለኝ። ያንን ለመርዳት የውጪሰው ኢትዮጵያዊያንን በማስተባበር ለመርዳት አሁንም ጥረቴን አላቆምም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል።
**እንዱዓለም ተፈራ**